# ከኢ.ዴአፓ-መድህን የተሰጠ መግለጫ

## ተስፋ ሰጪ እየሆነ ከመጣው የድርድር ሂደት የበለጠ ውጤት እንጠብቃለን

ባለፈው አመት አጋማሽ ላይ በኢህአዴግና በኢ.ዴአፓ-መድህን መካከል የተጀመረው ድርድር ከሞላ ጐደል አበረታች ውጤት እያሳየ ነው። ሁለቱ ፓርቲዎች የድርድር አጀንዳ እንዲሆኑ ይዘዋቸው ከቀረቡት ስምንት የመደራደሪያ ጉዳዮች ውስጥ በስድስቱ ላይ ለመወያየት ተስማምተዋል። ስምምነት ላይ ሊደረስባቸው ካልተቻለው ሁለት ጉዳዮች ውስጥ የመጀመሪያው በእስር ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅት አመራሮችና አባላት ጉዳይ ሲሆን ሁለተኛው በሰኔ ወር 1997 ዓ.ም እና በጥቅምትና በህዳር ወር 1998 ዓ.ም በዜጐች ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ ለማጣራት ስለ ተቋቋመው ኮሚሽን የአሠራር ሂደት ነው። በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ዙሪያ ፓርቲዎቹ ድርድር አካሂደው ለችግሮቹ የሚበጅ የፖለቲካ መፍትሄ ላይ ቢደረስ ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ጠቃሚ እንደሆነ በማመን ኢ.ዴአፓ-መድህን ሁለቱ ጉዳዮች በአጀንዳነት ቀርበው ድርድር እንዲደረግባቸው ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም በኢህአዴግ በኩል የመጀመሪያው ጉዳይ በፍርድ ቤት የተያዘ በመሆኑ፣ ሁለተኛው ጉዳይም በፓርላማው በተቋቋመ ኮሚሽን እየተጣራ ስለሆነ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመደራደር አልችልም የሚል አቋም በመያዙ ምክኒያት ስምምነት ላይ ሳይደረስ ቀርቷል።

በአጀንዳነት እንዲቀርቡ ስምምነት ላይ ከተደረሰባቸው ስድስት ጉዳዮች ውስጥ በመጀመሪያው ዙር ድርድር በሁለቱ ጉዳዮች ላይ ድርድር ተካሂዶ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል። በዚህ የመጀመሪያ ዙር ድርድር ኢ.ዴአፓ-መድህን በድርድር አጀንዳነት ካቀረባቸው ጉዳዮች ውስጥ፣ በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት ተቋማትና ባለስልጣናት ገዥውን ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በእኩልነት እንዲያገለግሉ፤ አናሳ መቀመጫ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በፓርላማው ውስጥ የመደመጥና አጀንዳ የማቅረብ መብታቸው እንዲከበር፣ የግንቦት 97ቱን ምርጫ ተከትሎ በፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የደረሱ ችግሮችን አጣርቶ መፍትሄ የሚሰጥ የጋራ ኮሚቴ እንዲቋቋም በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ ስምምነት ላይ ተደርሷል። የአገሪቱን ህገ-መንግስት በተመለከተም የፖለቲካ ፓርቲዎች ህገ-መንግሥቱን የማክበርና በህገ-መንግስቱ የመገዛት ግዴታ ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በህገ-መንግስቱ ውስጥ ያሏአቸውን የልዩነት ነጥቦች እራሱ ህገ-መንግስቱ በሚፈቅደው አግባብ ታግለው የማሻሻልም ሆነ የመለወጥ መብት ያላቸው መሆኑ በስምምነቱ እንዲካተት ተደርጓል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሁለቱም ፓርቲዎች የሚያካሂዱት የፖለቲካ ትግል ህጋዊና ሠላማዊ መስመርን ብቻ የተከተለ እንደሚሆን አረጋግጠዋል።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት የድርድር አጀንዳዎች የተደረገው የመጀመሪያ ዙር ውይይት ጥቅምት 7/99ዓ.ም ተጠናቆ ስምምነቱ ለሕዝብ ይፋ የተደረገ ሲሆን በሁለተኛው ዙር ድርድር ሁለቱ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም፣ በምርጫ ቦርድ ጉዳይ፣ ለፓርቲዎች ከመንግሥት ሊሰጥ ስለሚገባው የገንዘብ ድጐማና ስለ አጠቃላዩ ስምምነት የአፈፃፀም ስልት በአጭር ጊዜ ቀጣይ ድርድር ለማካሄድ ተስማምተዋል። በተለይም ገዥው ፓርቲ በሁለተኛው ዙር ድርድር በምርጫ ቦርድ ጉዳይ ላይ ለመደራደር ፈቃደኛ ሆኖ መገኘቱ የድርድሩን ሂደት የበለጠ አበረታች አድርጐታል። ከዚህ የመጀመሪያ ዙር ስምምነት በኋላም

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል በተደረገው ውይይት ሁለተኛው ዙር ድርድር በተሻለ የመቻቻል ስሜት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መግባባት ላይ ተደርሷል።

ኢዴአፓ-መድህን ይህ በጐ ጅምር የታየበት ድርድር በሁለተኛው ዙር ድርድር ለውይይት በሚቀርቡት ጉዳዮችም ይበልጥ ተጠናክሮ ከቀጠለና ለውጤት ከበቃ ለአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሂደት መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል ብሎ ያምናል። የግንቦት 97 ብሔራዊ ምርጫን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ብጥብጥ ምክኒያት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት የአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ወደተሻለ ደረጃ ይሸጋገር ዘንድ የድርድሩ ስኬታማነት ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖረው ኢዴአፓ-መድህን ያምናል። ሕዝባችን በአሁኑ ወቅት የሚያነሳቸው የዴሞክራሲና የመብት ጥያቄዎች በተሻለ መጠን መፍትሄ ያገኙ ዘንድም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከተናጠል አካሄድ ይልቅ የጋራ አጀንዳዎቻችንን በጋራ አቅርበን ከገዥው ፓርቲ ጋር በጠንካራ አቋም የምንደራደርበት ሁሉን አቀፍ የድርድር መድረክ ቢዘጋጅ የተሻለ አማራጭ እንደሚሆን ኢዴአፓ-መድህን እምነቱ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ይገልፃል። በድርድሩ ሂደት የሕዝባችን ጥያቄዎች መቶ በመቶ መልስ ያገኛሉ ብለን ከወዲሁ የማንገምት ቢሆንም በድርድሩ ሂደት በሚገኙት ውጤቶች ይበልጥ ተጠቃሚ እየሆኑ የድርድሩ ሂደት መልስ ላልሰጣቸው ተጨማሪ ጥያቄዎች ሠላማዊና ህጋዊ ትግሉን አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ አማራጭ መሆኑን በመገንዘብ ሕዝቡ ለድርድሩ ሂደት የበኩሉን ድጋፍ እንዲሰጥ ኢዴአፓ-መድህን በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል።

ÁäK%‰s!AeE lR›T lx!T×ùA!
\§MA ?Br-ብሔራዊነት ›§¥CN nW!

ጥቅምት 9/1999
አዲስ አበባ